# የባህርይ ጥናት(3)

## ጥናት አንድ (ሐዋ ሥራ 8፥9-25)

የጥናቱ ዓላማ፡- የእግዚአብሄር ነፃ ስጦታ በገንዘቡ ለመግዛት ከሞከረው ከሲሞን ስህተት በመማር የእግዚአብሄር ስጦታ ሁልጊዜ በነፃ እንደሆነ በመረዳት አመስግነን መቀበል መለማመድ ለመማር።

የጥናት መክፈቻ፡- የእግዚአብሄርን ነገር በገንዘቡ ወይም በጉልበቱ ወይም ደግሞ በማናቸውም ነገር ለመግዛት የሚሞክር ሰው አጋጥሞህ ያውቃል?

1. የሐዋ ሥራ 8፥9-25 በማንበብ ሲሞን ስለተባለው ሰው የምናውቃቸውን ነገሮች ዘርዝር።
2. ሲሞን አሁን ያለበትንና ሕይወትና ቀድሞ ይኖር በነበረበት ህይወት መሃል ምን ልዩነት ታያለህ?
3. ይህንን ክፍል ስታነብ ለምንድነው ዮሓንስና ጴጥሮስ ወደ ሰማርያ የመጡት?
4. በዛሬው ምንባብ እንደተመለከትነው ሲሞን ከእግዚአብሄር ሊያገኝ የፈለገው ነገር ምን ነበረ? ይህንን የፈለገውን ነገር እንዴት ሊያገኘው ሞከረ?
5. በጴጥሮስ አመለካከት መሠረት የሲሞን ሃሳብና ድርጊት እንዴት ነው ከእግዚአብሄር ሃሳብ ጋራ የሚጋጨው?
6. በቁጥር 27 የሰፈረውን የሲሞንን መልስ በመመልከት ስለ ንስሐው ያለህን አስተያየት ግለፅ።
7. ሰዎች በዚህስ ዘመን ከእግዚአብሄር የሚፈልጉትን ነገር ለማግኘት የሚጠቀሙባቸው አንዳንድ ሁኔታዎችን ተናገር። እግዚአብሄርስ ለዚህ ያለው መልስ ምን ይመስልሃል?
8. ከዚህ ክፍል በመማር ከእግዚአብሄር ስለ መቀበልና ስለ ፀሎትህ አይነት ምን ትማራለህ? ስለ እግዚአብሄር ባህርይስ ምን ከዚህ ምን ታያለህ?
9. የእግዚአብሄርን ሥጦታ በመልካም ባህርይህ ወይም በአገልግሎትህ ወይም በሌላ መንገድ ማግኘት የሞከርክባቸው ጊዜአት አሉ ወይ? ክስሞን ታሪክ የተማራችሁትን እርስ በእርሳችሁ ተከፋፈሉ።

# ጥናት ሁለት (ዮሐንስ 8፥1-11)

የጥናቱ ዓላማ፡- ክርስቶስ ሰዎችን ሁሉ የሚወድና የሚያከብር ማንንም የማይንቅ ስለሆነ የእርሱን ምሳሌ በመከተል እኛም ለሰዎች ሁሉ አክብሮትና ፍቅር እንዲኖረን እንዲሁም ማንንም እንዳንንቅ፥ እንዳናጣጥል ወይም በማንም እንዳንፈርድ ለመማር።
የጥናት መክፈቻ፡- በምትኖርበት ህብረተሰብ ውስጥ የተጣሉ ሰዎችን ታውቃልህ? እንደማይጠቅሙና እንደማያስፈልጉ ህብረተሰባችን የሚነግረን ምን ዓይነት ሰዎችን ነው?

1. ዮሐንስ 8፥1-11 ያለውን ክፍል በማንበብ በምንዝርና የተያዘችው ሴት ወደ ክርስቶስ ልትመጣ የቻለችበት ሁኔታዎች ምንድናቸው?
2. ፈሪሳውያን ይህንን ክስ ያቀረቡት የራሳቸውን ዓላማ ለማስፈፀም መሆኑን የሚጠቁመን ነገር አለ ወይ?
3. በዘሌዋውያን 20፥10 ያለውን ቃል ተመርኩዘው ይህንን ክስ ካቀረቡ ለምን ከእርሷ ጋራ ያመነዘረው ሰው አልተከሰሰም?
4. በቁጥር 6 ላይ የክስ ወጥመድ እንዳሰቡበት ይነግረናል። ይህ ለክርስቶስ ወጥመድ ሊሆን የሚችልበት በምን መንገድ ነው?
5. ክርስቶስ ይህች ሴት የተጠላችና የማትረባ እንዳልሆነች እንዴት አሳየ?
6. ጌታ የሱስ ለምን ይመስልሃል ለከሳሾችም ለተከሳሽዋም ስለ ሐጥያት የተናገረው?
7. ሰዎች እንደማትረባ መወገርና መጣል እንዳለብህ ሲያሳስቡህ ክርስቶስ ግን ዋጋ እንዳልህ ሲነግርህ በህይወትህ ምን ዓይነት ልዩነት ያመጣል?
8. ሰዎችን ለራሳችን ዓላማ መክሰስ ምን ዓይነት ጉዳት በህይወታችንና በቤተ ክርስትያን ሊያመጣ ይችል ይመስልሃል? ከዚህስ ለህይወትህ የምታስቀረው ትምህርት ምንድነው?

## ጥናት ሶስት (ሉቃስ 2፥21-40)

የጥናቱ ዓላማ፡- ሃናንና ስምዖንን በጥሩ ምሳሌነታቸው በመመልከት በጌታ ቤት ውስጥ እስከ ሽምግልናችን ድረስ እግዚአብሄርን እንድናገለግለው ለማበረታታት።

የጥናት መክፈቻ፡- በእግዚአብሄር ቤት በእድሜ የሸመገለ ሰው የምታውቀው ሰው አለ? አንተስ በሽምግልናህ ምን ዓይነት ሰው መሆን ትመኛለህ?

1. ሉቃስ 2፥21-40 ይነበብ። በምንባቡ መሠረት ሕፃኑ ኢየሱስና ቤተሰቦቹ ለምንድነው ወደ ኢየሩሳሌም የሄዱት?
2. ስምዖን የተባለው ሰው ክርስቶስን ለመገናኘት በምን መንገድ ተዘጋጅቶ ነበረ?
3. በቁጥር 29-35 መሠረት ስምዖን ስላለፈው ወይንም ደግሞ ስለሚመጣው ነገር የሚያውቀው እውነት ምን ነበረ?
4. "አሁን እኔን ባርያህን በሰላም አሰናብት" የሚለው የስምዖን ፀሎት እግዚአብሄርን ለመገናኘት ስላለው ዝግጅት ምን ያሳየናል?
5. ቁጥር 25 እና 37 ስታነብ በስምዖንና በሐና ሕይወት የምታየው ተመሳሳይነት ምንድነው? ይህችንስ ሴት እግዚአብሄር እንዴት ተጠቀመባት?
6. በዚህ ክፍል ከምታየው ከስምዖን ህይወት የምታደንቀውና በህይወትህ እንዲፈጸም የምትመኘው የሽምግልና ህይወት ምንድነው?
7. ቁጥር 36-40 በማንበብ የሃና ሕይወት አስቸጋሪ ቢሆንም በጣም ውጤታማ ነው ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን?
8. ለማንም ሰው ለማይቀረውና አንድ ቀን ለሚመጣው ሽምግልና አሁን በወጣትነትህ ማድረግ ያለብህ ዝግጅት ምን ይመስልሃል? በሚመጡትስ ሳምንታት በዚህ አንፃር ለመዘጋጀት ምን በማድረግ መጀመር ትችላለህ?

# ጥናት አራት (ዮሐንስ 9፥1-41)

የጥናቱ ዓላማ፡- በዚህ ጥናት ጌታ በህይወታችን የሰራውንና ከእርሱ ደግሞ በእምነት የሚገኙትን በረከቶች ማየት እንድንችል የእምነት አይኖቻችን መከፈት እንዳለባቸው ለመማር።

የጥናት መክፈቻ፡-

1. ዮሐ 9፥1-41 በህብረት ይነበብ። በቁጥር 1-5 ጌታ ኢየሱስ የተናገረው ቃል ይህ ዓይነ ሥውር ሰው እንዴት የሚረዳው ይመስልሃል? ቁጥር 6-12ትን በማንበብ ይህ ዓይነ ሥውር ስላለው እምነት ምን ትመለከታለህ?
2. ዓይነ ሥውሩ በቁጥር 13-34 ባለው ክፍል ውስጥ ከፈሪሳውያን ጋራ የነበረውን ትግልና የደረሰበትን ግፊት በራስህ ቃላት ግለጽ?
3. ቁ 2 "ይህ ሰው ዕውር ሆኖ እንዲወለድ ሃጥያት የሰራ ማን ነው" ቁ 29 "ይህ ሰው ከወዴት እንደሆነ አናውቅም" ቁ 39 "አንተ ሁለንተናህ በሐጥያት ተወለድክ" የዚህ አይነት ክሶች/ፍርዶች ለምን በጣም የሚጎዱ ይመስልሃል?
4. በዚህ ክፍል ውስጥ ሐጥያት በምን መንገድ ተገልጿል? ለአንተ ይህ ትክክል ይመስልሃል ወይ?
5. በፈሪሳውያን መካከል ለምንድነው መለያየት የመጣው?
6. የዚህ ሰው የእምነትና የመንፈሳዊ አይኖች አከፋፈት ደረጃ ቁ 11-12, ቁ 17, ቁ 27, ቁ 30-33, ቁ 36-38 አወዳድር።
7. በቁጥር 39-41 ያለውን የክርስቶስን ንግግር ለፈሪሳውያን አስረዳ ብትባል እንዴት ትገልጸዋለህ?
8. የአንተስ የእምነት ዓይኖችህ አከፋፈት ደረጃው ከዚህ ሰው ጋራ አነፃፅር። መለወጥ የሚያስፈልገው ከሆነ በዚህ ሳምንት ለጌታ ንገረው።

# ጥናት አምስት (ፊልሞና)

የጥናቱ ዓላማ፡- በአናሲሞስና በፊሊሞና እንዲኖር ሐዋርያው የሚጥረውን የወንድማማችነት ስሜት በመመልከት በመሐላችን ያሉትን ልዩነቶች አስወግደን አንድነታችንን አብዝተም ማጠናከር እንደሚገባን ለመማር።

የጥናት መክፈቻ፡- በጌታ ቤት ለመውደድና እንደ ወንድም/እህት ለመቀበል የሚያስቸግሮት ሰው ገጥሞት ያውቃል? ለዚህ ችግሮ መፍትሄ እንዴት አገኙለት?

1. የፊልሞና መልዕክት 1-25 ይነበብ የሐዋርያውን ሰላምታ ስታነብ በጸሐፊውና በተጻፈለት ሰው መሃል ስላለው ግንኙነት ምን ትመለከታለህ?
2. ቁጥር 8-21ትን በማንበብ አናሲሞስ ምን አይነት ሰው እንደሆነ ትረዳለህ?
3. ሐዋርያው ጳውሎስ ለፊልሞና ያለውን ፍቅር እንዴት ነው የገለጸው? ለአናሲሞስስ ያለውን ፍቅሩን እንዴት ታያለህ?
4. “አናሲሞስ” ማለት የስሙ ትርጉም የሚጠቅም ማለት ነው። ጳውሎስ በቁ 11 ላይ ለፊልሞና እንዳልጠቀመው ይናገራል። አሁን ግን የሚጠቅም ሰው እንደሆነ ለፊልሞና ያስረዳል። እንዴት ነው ይህ ሰው ዛሬ ጠቃሚ የሆነበት ምክንያት?
5. በፊልሞና መልዕክት ውስጥ በተጠቀሱት ሰዎች መሃል በሶሻልም፥ በኤኮኖሚና በጆግራፊ ሰፊ ልዩነት ያለ ሲሆን ይህንን ግን ለልዩነታቸው እንዳልተጠቀሙበት እናያለን። ይህ ሁኔታ ለእኛስ በዚህ ዘመን ላለነው አማኞች ምን ያስተምረናል?
6. በህይወትህ በወንድሞች አንተ የታቀፍክበትና እንደተቀበሉህ የተሰማህ ልምምድ ካለህ አካፍል። ከሆነስ በህይወትህ ምን ለውጥ አምጥቷል?
7. በዚህ ጥናት ውስጥ የጳውሎስ ትዕዛዝ ሌሎችን እንዴት መቀበል እንዳለብህ ምን ያስተምርሃል?

# ጥናት ስድስት (ዮሐንስ 11፥1-44)

የጥናቱ ዓላማ፡- ኢየሱስ ክርስቶስ የማርያምንና የማርታን ውድ ወንድም ከመቃብር ማውጣት እንደቻለ የእያንዳንዳችንንም ሞተብን ያልነውን ነገራችንን ሊያስነሳልን እንደሚችል ለመማር።

የጥናት መክፈቻ፡- ሞት ሁልጊዜ ለምን አዲስ ይሆንብናል?

1. ዮሐ 11፥1-44 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ። በቁ 1-16 ውስጥ ማርያም፥ ማርታ፥ አልዓዛርና ጌታ የሱስ ስለነበራቸው ግንኙነት ምን ትረዳለህ?
2. ራስህን ከደቀመዛሙርቱ እንደ አንዱ ቁጠርና ከዚህ ተዓምራት በኋላ ወደ ቤትህ ስትሄድ በአዕምሮህ ምን ምን ጥያቄ ይመላለስብህ ይመስልሃል?
3. የጌታ ቃል የደቀመዛሙርቱን ፍርሃት እንዴት ያረጋጋ ይመስልሃል?
4. በቁጥር 17-37 ውስጥ በምታነበው የሃዘንና የለቅሶ ቤት መሆኑን በምን በምን ምልክት ታያለህ?
5. አንተ የምትወደውና የምታቀርበው ወዳጅ ቢለይህ ምን ዓይነት እርዳታ ቢደረግልህ ነው ሃዘንህን የሚያስረሳህ ሃዘንህን የሚያቃልልህ?
6. ቁጥር 21-27ትን አንብብ። የጌታ የሱስ ቃል(ቁ 25) ለማርታ ምን አይነት መጽናናት የሰጣት ይመስልሃል? ለማርያምስ ቁጥር 23-37 ምን ዓይነት መጽናናት የሆናት ይመስልሃል?
7. ቁጥር 21, 32, 37ትን በማንበብ ሰዎቹ ስለ ጌታ የሱስ ችሎታና ስለማንነቱ ስላላቸው እውቀት ምን ትረዳለህ?
8. በዚያ ሥፍራ ኖረህ በመቃብሩ ስፍራ የተከናወነውን ነገር የመመልከት ዕድል ኖሮህ ቢሆን(ቁ 38-44) ምን ዓይነት ሥሜት ይሰማህ ነበር? ምን ዓይነትስ ጥያቄ ወደ ዓዕምሮህ ይመጣ ይመስልሃል?
9. ከዚህ ክፍል ለህይወትህ ምን ትማራለህ? በዚህ ዘመንስ የዚህ ዓይነቱ ተዓምራት ሊፈጸም ይችላል ብለህ ታምናለህ?